# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች

# ዳንኤልና ምስጢራዊው ሕልም



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Jonathan Hay

ያሻሽለው (አሻሽሎ የጻፈው): Mary-Anne S.

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጂ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

ንጉስ ናቡከደነጾር ሕልምን አለመ ፤ ይሔኛውም ሕልም እጅግ ረበሸው፡፡
በእግዚአብሔርም ኃይል ፣ ዳንኤልም ለንጉሱ የህልሙን ፍቺ አሳወቀው፡፡



ዳንኤል ያደረገው የመጀመሪያ ነገር ሕልሙን መግለጥ ነበረ፡፡ “አንተ ያየኸው የትልቅ ሀውልት ምስልን ነበረ ፤ አ! ንጉስ ሆይ ፣ ቅርጹም እጅግ አስደናቂ ነበረ፡፡”



“የሃውልቱ ራስ የተሰራው በወርቅ ነበረ” ሲል ዳንኤል ቀጠለ፡፡



“ደረቱና ክንዱ በብር
ተሰርቶ ነበረ፡፡”



“ወገቡና ሆዱ ደግሞ ከብሮንዝ የተሰራ ነበረ፡፡”



“እግሮቹ በብረት
የተሰሩ ነበሩ ፤ ውስጥ
እግሩ በግማሽ ከብረትና
በግማሽ ደግሞ ከሸክላ
ተሰርቷል፡፡”



ምስሉን ለንጉሱ ከገለጠው በኋላ ፣ ዳንኤል
የተቀረውን ሕልም መናቀሩን ቀጠለ፡፡



ዳንኤልም ለንጉሱ እንዲህ አለው ፣
“ምንም አይነት እጅን ሳይጠቀሙ
ድንጋይ ሲሰበር አየህ፡፡”



“ድንጋዩም ምስሉን በብረትና
በሸክላ በተሰራ እግሩ ላይ አረፈ
እና ሰባበረው፡፡”



“ምስሉም ወደ አሸዋነት ተቀየረ እና በነነ፡፡”
ዳንኤልም አቆመ፡፡ ድንጋዩም ወደታላቅ
ተራራነት ተቀይሮ ምድሪቱን ሞላት፡፡



ንጉሱም ተደነቀ፡፡ በትክክሉ ያለመው ይሄንኑ ነገር ነበረና፡፡ ዳንኤል ይሄንን እንዴት ሊያውቅ ቻለ? እግዚአብሔር ስለነገረው ብቻ፡፡ ዳንኤልም ንጉሱን ናቡከደናጾርን ሕልሙ ምን እንደሆነ አሳወቀው፡፡





“የሰማይ አምላክ ለአንተ
ንግስናን ፣ ኃይልን ፣
ጥንካሬንና ክብርን
ሰጥቶሃል፡፡” “አንተ
ያኛው የወርቅ ራስ ነህ፡፡”

ዳንኤልም ለንጉሱ ያሔኛው ወርቃማ
ንግስና እንደሚያበቃት ነገረው።
የምስሉ የብሩ ክፍል የሚያሳየው
ደካማ የሆነ መንግስት
እርሱን እንደሚተካው
ነው። ብሮንዙም
እንገና ሌላ መንግስት
እንደሚመጣ ነው።
ብረቱና ሸክላው
እንደገና አራተኛ
መንግስት እንዳለ
ማሳያ ነው።



ዳንኤል ለንጉሱ የነገረው
የመጨረሻው ነገር ይሔ ነበረ፡፡
“የሰማያት አምላክ ለዘላለም
የማይጠፋን መንግስት
እንደሚመሰርት ነው፡፡”



ንጉሱም ዳንኤል ስለ ሕልሙ
እንዲያውቅና እንዲገነዘብ
እግዚአብሔር ብቻ እንደሚረዳው
አወቀ፡፡ ናቡከደነጾርም ዳንኤልን
በኃብት ሁሉ ባረከውና በመንግስቱ
ላይ እጅግ የሚጠቅም
ሰው አድረጎ ሾመው፡፡



የመጀመሪያው
የሁለተኛው እና
የሶስተኛው
መንግስታት
መጥትው
ሔዱ፡፡



የእግዚአብሔር
ም መንግስት
ከአራተኛው
መንግስት በኋላ
መጣ፡፡ መሲሁ
በምድር ላይ
ይነግሳል ፤
ያም ቶሎ
ይሆናል፡፡

# ዳንኤልና ምስጢራዊው ሕልም

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዳንኤል 2

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16